1 ኛ ዓመት ቁጥር 14
1st Year No. 1

ባሕር ዳር ሰኔ 24 ቀን 1988 Bahir
Dar 1st JULY 1996

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴምክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.BOX

ማውጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 14/1988 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 7	Proclamation 14/1996 A proclamation to provide for the Establishment of an Agency for he Administration of Rented Houses Page 7

አዋጅ ቁጥር 14/1988
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፣

የቀድሞ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በአዋጅ ቁጥር

Proclamation 14/1996
Aproclamation to provide for the Establishment of an Agency for the Administration of Rented Houses.

Where as believing that

59/68 ተቋቁሞ ከፍቷቸው የነበሩት የሰሜን ምሥራቅና የሰሜን ምዕራብ ቀጠና ጽ/ቤቶች ያስተዳድራቸው የነበሩትን ቤቶች በአንድ ድርጅት እንዲመሩ ማድረግ የቤት ችግርን ለመፍታት የበለጠ አቅም እንደሚፈጥርና አሁን ያሉትን የአስተዳደር ችግሮች ለመፍታት እገዛ እንደሚያደርግ በመታመኑ በተበታተነና አነስተኛ በሆነ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይመራ የነበረውን ነባር ድርጅት የጠራ ዓላማና ሰፊ አቋም እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፣

አሁን ያሉትን ቤቶች በአግባቡ በመጠበቅ ከመንግስት ልዩ ወጪ ሳይጠይቅ የኪራይ የቤቶችን እየሰራ የሚያከራይ ድርጅት መፍጠር መንግስት ሀብቱንና ጉልበቱን አንገብጋቢ ወደ ሆኑ የልማት ተግባራት እንዲያተኩር ስለሚያስችለው፣

አሁን በሁለት ቀጠና ጽ/ቤቶች ሥር የሚተዳደሩትን ጠንካራ የማስተዳደር መብት ባለው የገበያ ሕግጋትን ተከትሎና የኪራይ ዋጋን የማረጋጋት ሚና ይዞ በሚሰራና የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ባለው አካል እንዲተዳደር ማድረግ አስፈላጊነቱን በመገንዘብ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 እና 3/10 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ፣

ጠቅላላ፣

1/ አጭር ርዕስ፣

ይህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 14/1988 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፣

1. "ድርጅት" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ነው።
2. "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው።
3. "ከ.ቤ.አ.ድ." ማለት በአዋጅ ቁጥር 59/68 የተቋቋመው የማዕከላዊ መንግስት ድርጅት ነው።
4. "ቀጠና ጽ/ቤት" ማለት የሰሜን ምዕራብ እና የሰሜን ምሥራቅ ቀጠና ፍ/ቤቶችን ነው።

ክፍል ሁለት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት መቋቋም፣ ተጠሪነት፣አደረጃጀትና ዓላማዎች፣

3 ስለ ድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት፣

1. የሰሜን ምዕራብ ቀጣናና የሰሜን ምስራቅ ቀጠና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ጽ/ቤቶች ከዚህ ከኃላ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እየተባለ የሚጠራ እራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ በዚህ

administering those houses that had been under the administration of the zonal offices of, North East and North West opened by the former agency for the administration of rented houses, established by proclamation number 59/68, under an agency create capacity in allevating housing problems and also contribute in solving the existing administrative problems, and thus it has become necessary to make the dispersed and small branch offices of the former agency in to an agency having clear objectives and far reaching standings.

Where as, realising that to create an agency that properly maintain the existing houses and construct the same for rent with out requiring special expenditure enables the stat to concentrate its properties and man power to wards the most needy development activities.

Where as, realising that it is necessary to administer the houses which presently are under the adminstration of the two zonal offices by an agency that have its own juridical personality and the right of a strong administrative discretion working following the market laws and playing the role of stabilizing housing rents.

Now there fore in accordance with article 49 sub article 3(1) and 3(10) of the constitution of the council of the Amhara National Regional State here by proclamied as follows.

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as" the Agency for that adminstration of Rented Houses of the Amhara National Regional State establishment Proclamation Number 14/1996"

አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ድርጅቱ የሰሜን ምዕራብ እና የሰሜን ምሥራቅ ኪቤአድ ቀጠና ጽ/ቤቶችን አጠቃላይ ንብረት መነሻ ካፒታሉ አድርጉ ተቋቁሟል፣
3. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና የክልሉ መንግስት ለሚሰይመው የሥራ አመራር ቦርድ ይሆናል።

4. <u>የድርጅቱ አደረጃጀት፣</u>

1. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።
2. ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፣

5. <u>የድርጅቱ ዓላማ</u>

የድርጅቱ ዓላማ በይዞታው ሥር ያሉትን የኪራይ ቤቶች በአግባቡ ማስተዳደር ማከራየትና ተጨማሪ ኪራይ ቤቶችን በመሥራት የሕዝቡን የቤት ችግር ለማቃለል እገዛ ማድረግ ነው።

<u>ክፍል ሶስት፣</u>

<u>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ጠቅላላ ስልጣንና ተግባር እና ድርጅታዊ አቋም፣</u>

6. <u>ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር፣</u>

ድርጅቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ.በስሙ የመክሰስ የመከሰስ ገንዘብ የመበደር እንዲሁም ውል የመግባት፣

ለ.የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትና ባለ ይዞታ የመሆን ለሌላም የማስተላለፍ፣በቁጥጥሩ ሥር የሚገኙትን ቤቶች የማከራየት፣ኪራያቸውንም በጊዜው የመሰብሰብና ቤቶቹን የመጠበቅ፣የማደስና አስፈላጊ ሲሆንም ፈርሰው በሌላ እንዲተኩ የማድረግ፣

ሐ. አከራይ የሚፈጽመውን ግዴታ ሁሉ የመፈጸም እና ተከራይ የገባውን ግዴታ ሁሉ የማስፈጸም፣

መ. የቤት ኪራይ መጠን እንደየደረጃው እንዲወሰን ጥናት የማድረግና በቦርዱአማካኝነት ለክልሉ መንግስት አቅርቦ የማስወሰን፣

ረ. አዳዲስ ቤቶችን የመሥራትና የማከራየት፣

7. <u>ድርጅታዊ አቋም፣</u>

ድርጅቱ፣

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. በክልሉ መንግስት ሥ/አ/ኮ/ የምሾም አንድ ሥራ አስኪያጅ፣
3. ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈለጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል።

2. <u>Definitions</u>

Unless the context requires other wise in this proclamation

1. **"Agency" means agency for the adminstration of Rented Houses of the Amhara National Regional State established Pursuant to this proclamation**
2. **"Board" means the managing board of the agency for the adminstration of rented houses of the Amhara National Regional State established pursuant to article 8 of this proclamation.**
3. **"A.A.R.H" means the central Government Agency established by proclamation Number 59/68.**
4. **"Zonal office" means the zonal offices of North west and North east.**

<u>PART TWO</u>

<u>Establishment, accountability, organization and objectives of the agency for the adminstration of Rented houses of the Amhara National Regional State</u>

3. <u>Establishment and accountability of the agency:</u>

1. **Zonal offices of North west and north east offices for the adminstration of rented houses here in after refered to as "agency for the adminstration of rented houses of the Amhara National Regional State is here by established as an autonomous agency having legal personality under this proclamation.**
2. **The agency is established by making the total assets of the zonal office of the North West & North East Agency for the Administration of Rented Houses as it's initial**

ክፍል አራት፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ

8. የስራ አመራር ቦርድ አባላት፣አወቃቀርና የስራ ዘመን፣

1. የሚዋቀረው የሥራ አመራር ቦርድ ከአምስት ያላነሱ አባላት ይኖሩታል፣
2. የቦርዱ አባላት በክልሉ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሰየማሉ፣
3. የሥራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፣
4. የቦርዱና የአባላት የስራ ዘመን በክልሉ መንግስት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
5. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አበል በክልሉ መንግስት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ ይወሰናል።

9. የቦርዱ የስብሰባ ስርዓት፣

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከቦርዱ አባላት 2/3 ኛው በስብሰባው ከተገኘ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

10. ስለተጠሪነት

የቦርዱ ተጠሪነት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

11. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር፣

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ. የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ በመምረጥ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያሾማል፣

ለ. ለሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑትን የስራ ኃላፊዎች፣ የደረጃ ዕድገት፣ቅጥር፣ዝውውርና ስንብት ያጸድቃል፣

ሐ. ድርጅቱ የሚመራበት አጠቃላይ ፖሊስ በማመንጨት ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

አቅርቦ ያስፀድቃል። በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፣

መ. የድረጅቱን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከ . ..

ሠ. ድርጅቱ በሰው ኃይል፣በመሳርያና በሥራ አመራር የሚጠናከርበትን መንገድ ያስጠናል፣ጥናቱንም ጠቃሚ ሆኖ

Capital

3. The agency being established for ın specified period of time shall be accountable to the executive committee of the Amhara National Regional State. and the managing board assigned by the same.

4. Organization of the Agency

1. The head office of the agency shall be in Bahir Dar

2. The agency may have branch offices to be established in any places as may be necessary.

5. Objective of the agency

The objective of the agency shall be to appropriately administer and rent houses under its possession and there by assist to alleviate the housing problem of the public by constructing additional houses.

PART THREE

General duties and Powers, and Organizational structure of the Agency for the Administration of rented Houses of the Amhara National Regional State

6. General powers and duties

The agency shall have the following powers and duties to:

A. Sue and be sued in its own name, loan money as well as enter in to contract,

B. Own, posses and transfer movable and immovable properties, rent houses under its possession, collect their fees periodically, keep and maintain the houses or do away with and replace them by otheres when necessary.

C. Execute on the obligation of the leaser and cause the execution of the obligation entered by the lees.

D. Conduct studies on the basis of standards, for determination of house rent fee and through the board present the

ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ረ. የድርጅቱ ንብረት በአግባቡ መያዙን፣የገንዘብና የሰው ኃይል አጠቃቀሙም የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዓላማዎች እንዲሁም የድርጅቱን ዓላማ ለማስፈጸም ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ሰ. በድርጅቱ የሚቀርቡትን ጉዳዩች እየመረመረ ውሳኔዎችን ያፀድቃል፣

ቀ. በድረጅቱ የሚቀርቡለትን የኪራይ ማሻሻያ ጥናት እየገመገመ ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስፀድቃል።

በ. በወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምታቸው እስከ ብር 500,000 የሆኑ ንብረቶችን በተመለከተ ሽያጭ፣ግዥ፣ማፍረስና ግንባታ፣ያጸድቃል፣

ተ. የመካከለኛ ጊዜ ብድሮችን ያጸድቃል፣እንዲሁም የረጅም ጊዜ ብድሮችን እያስጠና ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስወስናል፣

ቸ. ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፣

ክፍል አምስት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣ስልጣንና ተግባር

12. የሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር፣

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን፣በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ የድርጅቱን የሥራ መዋቅር፣ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ በማቅረብ ያጸድቃል፣ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
3. የድርጅቱን ገንዘብ ለማንቀሳቀስ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣
4. የድርጅቱን የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣በጀት የሥራ ኘሮግራም እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ሲጸድቅም በተግባር ላይ ያውላል።
5. ለሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑ የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና ስንብት በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያጸድቃል፣
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰው

እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ሕግና በድርጅቱ የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ያሰናብታል፣

7. ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ እንዲሆን ያደርጋል በስራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፣
8. የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ያስፈጽማል።
9. የቤት ኪራይ በአግባቡ መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፣
10. ድርጅቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነትና ውለታ ሁሉ መ/ቤቱን ይወክላል፣
11. ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለሥራ አመራር ቦርድ የየሩብ ዓመት፣ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣
12. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

same for the decision of the regional state.

E. Construct and rent new houses.

7. Organizational Structure

The Agency shall consist of:

1. **A managing board**
2. **A manager to be appointed by the executive commttee of the regional state.**
3. **Other responsible personnels and employees necessary on each level.**

PART FOUR

The managing Board of the Agency for the Adminstration of Rent of houses of the Amhara National Regiona State

8. Members, organization and term of services of the managing board

1. **The managing board to be established shall consist of not less than five members**
2. **The member of the board shall be assined by the executive committee of the regional tate**
3. **The managing board shall have achairman and secretary.**
4. **The term of service of the board and its members shall be determined by a regulation to be issued by the executive committee of regional state**
5. **The allowance of the members of the mannaging board shall be determined by the executive committee of the regional state as may be necessary.**

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፣

13. የድርጅቱ የበጀት ምንጭ እና የበጀት ዓመት፣

ሀ. የድርጅቱ በጀት የሚገኘው ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች ይሆናል፣

1. ድርጅቱ ከሚሰበሰበው የቤት ኪራይ፣
2. ለካፒታል በጀት እንደአስፈላጊነቱ ከባንክና ከሌሎች ድርጅቶች ከሚገኝ ብድር እና
3. ከሌሎች፣

ለ. የድርጅቱ የበጀት ዓመት ከመንግስት የበጀት ዓመት ጋር አንድ ነው።

14. የድርጅቱ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር፣

1. የድርጅቱ ሠራተኞች ቅጥር እና አስተዳደር በአሰሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደ አስፈላጊነቱ የራሱን የሰራተኛ ማስተዳደርያ ደንብ ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

15. የሂሳብ መዛግብት፣

1. ድርጅቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፣
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የድርጅቱን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝን በተመለከተ ቦርዱ ተቀባይነት ያላቸው የሂሳብ አሠራሮችን ሊጠቀም ይችላል።

16. የሂሳብ ምርምር፣

የድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች
ኦዲተር ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች ... ይመረመራሉ።

17. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ፣

የሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምሥራቅ ኪቤአድ ቀጠና ጽ/ቤቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

18. ስለ ትርፍ አከፋፈል፣

የድርጅቱን የተመረመረና የተጣራ ትርፍ አከፋፈልን በሚመለከት ቦርዱ ለክልሉ መንግስት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለውሳኔ ያቀርባል።

19. የኃላፊነት ወሰን፣

ድርጅቱ በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጠቅላላ ያለው ንብረት እስከሚሸፍነው ድረስ ብቻ ነው።

20. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

9. Meeting procedure of the board

1. The board shall convene its regular meeting once in every three months, However extra ordinary meetings shall be held at any time as may be necessary.
2. The presence of 2/3rds of a member of the board shall constitute a quorum.
3. Decision of the board shall be passed by simple majority vote; however in case of a tie the chair person shall have a casting vote.
4. With out prejudice to the provision of this article, the board may adopt its own rules and meeting procedures.

10. Accountability

The Board shall be accountable to the excutive committee and the head of the Amhara National regional state.

11 powers and duties of the board

The board shall have the following powers and duties to:

A. Select and present the manager of the agency for appointment to the excutive committee of the region.
B. Approve the promotion emplyment, transfer and dismisal of heads accountable to the manager.
C. Initiate and present the general guiding policy of the aency to the executive committee of the region for approval and follow up its implementation.
D. Approve the budget and action plan of the agency and follow up its implementation
E. Cause the study of the mechanisms by which the agency is going to be strengthen in man power equipment and management and implement the same when it found

21. ደንብ የማውጣት ስልጣን

ቦርዱ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦችና መመሪያዎች የማውጣት ስልጣን አለው።

22. አዋጁን ስለማሻሻል ወይም ስለ መሻር

ይህን አዋጅ የማሻሻል ወይም የመሰረዝ ሥልጣን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው።

23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በገዘከረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ሰኔ **24/1988**
የአማራሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት።

vital.

F. Insure the proper handling of the property of the agency and its utilization of finance and man power for efficient execution of the economic and social objective of the region as well as the objective of the agency.

G. Examine and pass decisions up on cases presented to it by the agency

H. Submit for approval to the executive committee of the region up on evolution of the rent amendment studies presented to it by the agency.

I. Approve concerning the sale, purchase, demolition and construction of such properties whose current market value is estimated up to 500,000 birr.

J. Approve medium term loans and also cause studies on long term loans and present the same for approval

K. Submit periodic reports to the executive committee of the region.

PART FIVE

Powers and duties of the manager of the Agency for the Adminstration of rented houses of the Amhara National Regional State

10. Power and Duties of the manager.

The manager of the agency shall in addition to the powers and duties vested in the agency as enumerated under article 6 of this proclamation have the power and duties to:

1. Direct, administer and supervise the activities of the agency

2. Organize the office, prepare and submit to the board for approval the organizational structure, salary and allowances of the agency, and follow up its implementation

3. Open bank account to run the finance of the agency.

4. Prepare and submit to the board ,short, medium and long

term plan, budget and action plan of the agency, and implement the same up on approval

5. **Submit to the board for approval, concerning the employment, assignment and dismissal of heads of the agency accountable to the general manger.**
6. **With out prejudies to the provision of sub**

Article 5 of this article, employee, administer, promote and dismiss its employees in accordance with the appropriate law and administrative regulation of the agency.

7. **Cause, expenditure in accordance with the approved budget and plan of action of the agency, and supervise the implementation of the same.**
8. **Excite, and cause the execution of the decision of the board**
9. **Supervise, the proper collection of house rent**
10. **Represent the agency in its dealings with other third parties.**
11. **Prepare and submit quarterly and annual activity performance and financial reports, to managing board and the executive committee of the region.**
12. **Perform such other duties assigned by the boare**

PART SIX

Miscellaneous Provisions

13. Budget source and budget year of the Agency

A. **The budget of the agency shall be drawn from the following financial sources.**
   1. **House rent collected by the agency.**
   2. **Loans obtained from bank sand other agencies for the purpose of the capital budget as may be necessary and**
   3. **From others.**

B. The budget year of the agency shall be the same with the budget year of the government.

14. <u>Employment and administration of the staffs of the agency</u>

1. Employment and administration of the staff of the agency shall be effected in accordance with labour proclamation.

2. With out prejudice to the provision of sub article 1 of this article than agency shall prepare its employment administrative regulation as may be necessary, and up on approval implement the same.

15. <u>Books of accounts</u>

1. The agency shall keep appropriate & complete books of accounts

2. The board shall utilize accepted accounting procedures, concerning the handling of the books of accounts and financial documents of the agency, as may be necessary.

16. <u>Auditing</u>

The books of accounts and financial document it's of the age nay shall beady teed, by the auditor general or external or external auditor assigned by the board.

17. <u>Transfer of right and obligation</u>

The rights and obligation of zonal offices of north west and north east Agencies for the administration of rented house is here by transfer to the agency pursuant to this

proclamation.

18. Profit payment

The board shall present to the executive committee of the regional state for decision concerning the payment of the audited net profit of the agency

19. Scope of liability

The agency shall be held liable only to the extent of its total assets.

20. Inapplicable laws

Any law which is in consistent with this proclamation shall not apply to matters provided for in this proclamation

21. Power to issue regulation

The board shall have the power to issue regulations and directives necessary for the purpose of implementation of this proclamation

22. Power to amend or repeal this proclamation

Power to amend or repeal this proclamation shall only belong to the council of the Amhara National Regional State

23. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Ziker high gazette.

Done at Bahir Dar
This 1st day of July 1996
Council of the amhara national Regional state.